P.O. Boxes: 4916, 2003EX, Haarlem, The Netherlands; 56281, London, N4 9BH, UK

# ወያኔን ከነእብሪቱ ለማስወገድ ውጤታማና ዘላቂ ትብብር እንመሥርት!

የግንቦት 7 ርዕሰ አንቀጽ ቁጥር 111

የዓለም ታላላቅ ሚዲያዎች በአንድ ድምፅ ወያኔን "አፈርንብህ" እያሉት ነው:: ምዕራባዊያን በተለይም መንግሥታቱ በወያኔ ላይ የተወሰነ ተስፋ ነበራቸው:: ከመለስ በርካታ ምላሶች አንዱ በዚህ ተግባር ሰልጥኗልና ለዘመናት በጮሌነት ሲያታልላቸው ኖሯል:: ዘንድሮ - በ2002 ዓ.ም. በምርጫ ስም ተፈጽሞ በዓይናቸው ያዩት ነገር በጆሮዓቸው ሲሰሙት የቆየውን ፈጽሞ አይመስልም:: በዚህም ምክንያት ምዕራባዊያን ሚዲያዎች በወያኔ ላይ የተሰማቸውን እፍረት በዝርዝር እየነገሩን ነው:: ባለፉት ጥቂት ሳምንታት ውስጥ ብቻ ኒዮርክ ታይምስ፣ ሬውተር፣ አሶሼትድ ፕሬስ፣ ሎስ አጀለስ ታይምስ፣ ብሉምበርግ፣ ዘ አትላንታ፣ ቪኦኤ፣ ቢቢሲ እና ሌሎች በርካታ የዜና አውታሮች በወያኔ አሳፋሪ የምርጫ ተውኔት ላይ ጽፈዋል፤ ተችተዋል:: "የበሰበሰ ዝናብ አይፈራም" እንዲሉ ወያኔ "የምርጫው ውጤት ትክክለኛ ነው ብላችሁ ተቀበሉኝ፤ አለበለዚያ ግን እናንተንም ወዮላችሁ" እያለ ይዝትባቸው ጀምሯል:: የወያኔን ግብዝነት ከሚገልፁ በርካታ ነገሮች አንዱ ይኸ "ካፈርኩ አይመልሰኝ" ባይነቱ ነው::

ወያኔ በ97 ምርጫ ተሸንፎ በጉልበት ይዞ የቆየውን ሥልጣን በ2002 ህጋዊ ለማስመሰል የከወነው ትዕይንት የባሰውን እራቁቱን አስቀርቶት ከወዳጆቹ ጋር ሳይቀር አቀያይሞታል:: እሱ ግን አሁንም ስለ ምርጫው ውጤት ትክክለኝነትና ፍትሃዊነት ማብራሪያ ካልሰጠሁ ሞቼ እገኛለሁ እያለ ነው::

አንደኛው ክርክር "99.6 በመቶ አሸነፍክ መባሌ ቀርቶ የአጋር ድርጅቶች ድርሻ ተቀንሶልኝ 91.2 በመቶ ይባልልኝ" የሚል ነው:: መቼም ይኸ ክርክር ለውጭ አገር ሰዎች እንጂ ለእኛ ለኢትዮጵያዊያን የታለመ እንዳልሆነ ግልጽ ነው:: የአፋሩ አብዴፓ፣ የጋምቤላው ጋሕዴአን፣ የሶማሊው ሶሕዴአግ፣ የቤሻንጉል ጉሙዙ ቤጉሕዴአን እና የሀረሪው ሀብሊ በአንድ ሚዛን፤ የአማራው ብአዴን፣ የኦሮሞው ኦህዴድ እና የደቡቡ ደኢህዴን በሌላ ሚዛን አስቀምጠን ብናወዳድራቸው ሁሉም እኩል ገለባዎች መሆናቸውን እናውቃለን:: ከስማቸው መብዛት በስተቀር ሁሉም እኩል የወያኔ ተላላኪዎች መሆናቸው እነሱ ራሳቸው በተደጋጋሚ ያረጋገጡት ጉዳይ ነው:: ከአዲሱ ለገሠና አባዱላ ገመዳ፤ ከመሃመድ ድሪርና ከእስማኤል አሊ ሴሮ የቱ ለወያኔ ይቀርባል ብለን የምናወዳድርበት አንዳችም ምክንያት የለንም:: ስልቻ ቀልቀሎ፤ ቀልቀሎም ስልቻ ነው እንደተባለው ሁሉም የወያኔ ምንደኞች ናቸው፤ እነሱም ይህንን አይክዱም:: ሆኖም ይኸ ክርክር የምዕራባዊያንን ልብ ያለሰልስልኝ ይሆናል ብሎ

P.O. Boxes: 4916, 2003EX, Haarlem, The Netherlands; 56281, London, N4 9BH, UK

ገፍቶበታል:: የውስጡን ጉድ መረዳት ቢያስቸግራቸው እንኳን በእነሱ ዓይን ሲታይ በ99 እና በ91 በመቶ መካከል ያለው ለውጥ እምብዛም ነው::

ሁለተኛ የክርክር አቅጣጫ ደግሞ "ልማት አምጥቻለሁ፤ ይህ ደግሞ በራሱ ሕዝብን ቀጥቅጬ የመግዛት መብት ይሰጠኛል" የሚል ነው:: ነገር ግን ጠዋት ማታ የሚለፈፍለት የኢኮኖሚ እድገት የቁጥር ጨዋታ ውጤት መሆኑ ፈረንጆቹም መጠርጠር ጀምረዋል:: "የታል ምግቡ?" "የታል ሥራ?" "የታለ የጤናው አገልግሎት?" በተባለ ጊዜ ቁጥሮች አያድኑትም:: ወያኔ ደግሞ ለዚህ ማምለጫ "ፈጣን ልማት ስለሚፈጥራቸው ችግሮች" አዳዲስ ግኝቶችን እያስተዋወቀ ነው:: ወያኔ ፈጣን ልማት ባመጣው ችግር ምክንያት ሕዝብ ይራባል፣ ይጠማል፣ ይታረዛል፣ ይሞታል እያለ ልማት የሚባለው ነገር የሚፈራና የሚጠላ ክፉ መንፈስ እያደረገው ነው::

የወያኔ "ካፈርኩ አይመልሰኝ" ከሁሉም በላይ ጎልቶ የታየው ደግሞ "በድምፃችን ይከበር" ሰልፍ ላይ ነው:: የመለስ ዜናዊ የቀድሞ ወዳጆች ይኸን ሰልፍ በአደባባዩ ከተሰቀለው የመለስ ዜናዊ ምስል ጋር ሲቀርብላቸው የበርሊን ግንብ ከፈረሰ ሃያ አመት በኋላ ሌላ ተመሳሳይ ግንብ አዲስ አበባ እየተገነባ እንደሆነ እንዲታዘቡ አስችሏቸዋል::

"የአፈርንብህ" እና "ካፈርኩ አይመልሰኝ" ክርክሮችን ለጊዜው እዚሁ ላይ እናቁምና ወደ ራሳችን እንመለሰ:: መለስ በዚህ ምርጫ ግልጽ የሆነ መልዕክት ለሁላችንም አስተላልፎልናል፤ ንቀቱና እብሪቱን አሳይቶናል:: ምላሻችን ምንድነው?

በግንቦት 7 የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ እምነት ምዕራባዊያን የወያኔን እኩይ ተግባራት እየተረዱ መምጣታቸው መልካም ቢሆንም ነፃነታችንን ማስከበር የምንችለው እኛው ብቻ ነን:: የወያኔን እብሪት የሚመጥን የተባበረ ኃይል በአስቸኳይ መፍጠር ይኖርብናል::

አሁን የምንፈጥረው ኅብረት ደግሞ ከዚህ በፊት እንደተሞከሩ ኅብረቶች መንገድ ላይ የሚቆም መሆን የለበትም:: አሁን የምንፈጥረው ኅብረት ወያኔን አስወግደን በምትኩ በሕዝብ የተመረጠ መንግሥት እስከ ማቋቋም የሚደርስ አስተማማኝ ተቋም መሆን ይኖርበታል:: እንዲህ ዓይነቱ ውጤታማና ዘላቂ የሆነ ኅብረት ለመፍጠር በዝርዝር ጉዳዮች ላይ ሳይቀር በቂ ዝግጅት ሊደረግ ይገባል:: እንዴት መነጋገር እንዳለብን ሳይቀር መነጋገር ይኖርብናል:: ለዚህ የተቀደሰ ዓላማ ችሎታ፣ ሙያና ዝንባሌ ያላችሁ ወገኖቻችን በሙሉ ልባቸው ሊረባረቡበት ይገባል እንላለን::

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!